# መጽሐፈ ኢያሱ

መጽሐፈ ኢያሱ እስራኤላውያን የተስፋይቱን ምድር እንዴት እንደ ወረሱ የሚተርክ መጽሐፍ ነው:: በአምስቱ የሙሴ የኦሪት መጻሕፍት የተጀመረው፣ የእስራኤላዊያን የተስፋይቱን ምድር ለመውረስ ከግብጽ የመውጣት ታሪክ ፍጻሜ የሚያገኘው በመጽሐፈ ኢያሱ ነው:: ይህ መጽሐፍ በኢያሱ እንደተጻፈ ሲታመን፣ የ25 ዓመታት ያህል ታሪክ ያዘለ ነው::

ይህ መጽሐፍ የሚያተኩረው፤ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል የምንወርሰው በእምነት እንደሆነ በሚያሳዩ የድልና የውጊያ ታሪኮች ላይ ነው::

በዕብ. 6፡11-12 እና በዕብ. 4፡3 ላይ ያለው ቃል ይህንን መጽሐፍ ጥሩ አድርጎ ይገልጸዋል፤ «በእምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን::»

«እኛስ ያመንን ወደ ዕረፍቱ እንገባለን» ዕብ. 4፡3::

በአምስቱ የኦሪት መጻሕፍት፤ በተለይ ከዘጸአት ጀምሮ እስራኤላውያን በምድረ በዳ ሲፈተኑ እናያለን እንጂ ከአንድ ጊዜ በስተቀር፣ ሰይፍ መዘው የተዋጉት ውጊያ የለም:: ሰይፍ መምዘዝ የጀመሩት ዮርዳኖስ ወንዝ አጠገብ ወይም ወደ ተስፋይቱ ምድር ሊደርሱ ሲሉ ነው:: ከዚህ የምንማርው፤ የምድረ በዳ ሕይወት ራሳችንን (ሥጋችንን) የምናሸንፍበት ሲሆን ሥጋችንን ካሸነፍን በኋላ (የምድረ በዳውን ኮርስ ከጨረስን በኋላ) የተስፋይቱን ምድር ለመውረስ መንፈሳዊ ሰይፋችንን መዝዘን ከጠላት ጋር መዋጋትና ጠላትን ማሳደድ እንጀምራለን::

ይህ የኢያሱ መጽሐፍ በአዲስ ኪዳን ካለው ከኤፌሶን መጽሐፍ ጋር ብዙ ተመሳሳይነት ያለው መጽሐፍ ነው::

## በኢያሱና በኤፌሶን መካከል ያለው ተመሳሳይነት

1. ሁለቱም የሚያሳዩት የእግዚአብሔር ሕዝብ በነጻ ስለ ተሰጠው ርስት (በረከት) መውረስ ነው፡፡

ኢያሱ 20፡43 «እግዚአብሔርም ይሰጣቸው ዘንድ ለአባቶቻቸው የማለላቸውን ምድር ሁሉ ለእስራኤል ሰጠ፤ ወረሷትም ተቀመጡባትም፡፡»

ኤፌ. 1፡3 «በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፡፡»

ኤፌ. 1፡19 «... በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንደሆነ ... ታውቁ ዘንድ፤»

2. ሁለቱም መጻሕፍት፤ ይህንን ርስት የምንወርሰው በእምነት እንደሆነ ያስተምሩናል፡፡

ኢያሱ 1፡3 «ለሙሴ እንደነገርኩት፣ የእግራችሁ ጫማ የሚረግጠውን ቦታ ሁሉ ለእናንተ ሰጥቻለሁ፡፡» (በእምነት ካልረገጥነው አንወርሰውም ማለት ነው)

ኤፌ. 3፡12 «በእርሱም ዘንድ ባለ እምነታችን በኩል በመታመን ድፍረትና መግባት በእርሱ አለን፡፡»

3. የእግዚአብሔር ዓላማ፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ በኩል ክብሩና ሥልጣኑ እንዲገለጽ እንደሆነ ሁለቱም መጻሕፍት ይመሰክራሉ፡፡

ኢያሱ 4፡23-24 «... የዮርዳኖስን ውኃ ከፊታችሁ አደረቀ፡፡ ይኸውም የእግዚአብሔር እጅ ጠንካራ እንደሆነች የምድር አህዛብ ሁሉ እንዲያውቁ ... ነው፡፡»

ኤፌ. 3፡10 «ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት ለአለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ፤»

4. ሁለቱም መጻሕፍት ርስቱን ከመውረስ ጋር ውጊያ እንዳለ ያስረዳሉ፡፡ የኢያሱ መጽሐፍ፣ ከኢያሪኮ ጀምሮ እስራኤላዊያን ከብዙ አሕዛብ ጋር ተዋግተው ምድሪቱን እንደወረሱ የሚተርክ መጽሐፍ ነው፡፡

   የኤፌሶንም መጽሐፍ፤ በምዕ. 6፡10-18 በአዲስ ኪዳን ዘመን ያለንበት ርስት መንፈሳዊ ውጊያ ያለበት ህይወት እንደሆነ ያሳስበናል፡፡ «... የዲብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ፡፡»

## እስራኤላዊያን እንዲወርሱአት የተሰጣቸው የከነዓን ምድር፤ (እንዲሁም መንፈሳዊው ከነዓንም)

1. የእረፍት ምድር ናት

   ያልሠሩትን ከተሞች፣ ያልተከሏቸውን እርሻዎች የሚወርሱበት ምድር ነበረች (ዘዳ. 6፣10-12)

   «እኛስ ያመንን ወደ እረፍቱ እንገባለን» (ዕብ. 4፡3) የሚለው፣ የአዲስ ኪዳንን በክርስቶስ ኢየሱስ የተሰጠንን መንፈሳዊ ርስት በማስመልከት ነው፡፡

2. የበረከትና የሙላት ምድር ናት

   ማርና ወተት የምታፈስ ምድር ናት (ዘጸ. 3፡8) እኛም እንድንወርሳት የተሰጠችን መንፈሳዊ ርስት በሰማያዊ በረከት ሁሉ የተሞላች ናት፡፡ (ኤፌ. 1፡3) «በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፡፡»

3. የድል ምድር ናት

በምድሪቱ ላይ የነበሩትን አሕዛብ (ጠላቶች) ሁሉ በእግዚአብሔር እርዳታ ተዋግተው ድልን የሚጐናጸፉባት ምድር ናት። (ዘዳ. 7፡1-2)

ኤፌ. 6፡10-11 «... የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ....»

## የኢያሱ መጽሐፍ ዋና ሐሳብ፤

«የእምነት አሸናፊነት ነው።» 1ኛዮሐ. 5፡4

# በሦስት ዓቢይ ክፍሎች ይከፈላል።

ምድሪቱን መሰለል፤ ወደ ምድሪቱ ለመግባት መዘጋጀት፡- ምዕ. 1-5

መዋጋት፤ ተዋግቶ ጠላትን ከርስታቸው ማስወገድ፤ ምዕ. 6-12

መውረስ፤ የተስፋይቱን ምድር መውረስና ተደላድሎ መኖር፤ ምዕ. 13-24

ሀ. ምድሪቱን መሰለል፤ ለመውረስ መዘጋጀት፡- (ምዕ. 1-5)

ምዕ. 1፡ - ኢያሱ የእግዚአብሔርን መመሪያ ሲቀበል እናያለን። መመሪያውም የእግዚአብሔር ቃል ነው።

ኢያሱ 1፡7-8 «ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ አድርገውም በምትሄድበትም ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል። የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፤ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንና በሌሊትም አስበው የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም።»

በዚህ ምዕራፍ የምናየው የእምነት መሠረት የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ነው። ኢያሱ እምነቱን

በእግዚአብሔር ቃል ላይ ከመሠረተ፤ «በሕይወትህ ዕድሜ ሁሉ ማንም አይቋቋምህም» በማለት እግዚአብሔር ቃል ይገባለታል፡፡

## ምዕ. 2 ምድሪቱን ስለ መሰለል ያወሳል

ምዕ. 2፡1 «ሄዳችሁ ምድሪቱንና ኢያሪኮን እዩ ብሎ ከሰጢም ሁለት ሰላዮች በስውር ላከ፡፡»

ይህ ምዕራፍ የሚያሳየን <u>የእምነትን ጥንቃቄ</u> ነው፡፡ እምነት ዕውር ወይም ጭፍን አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ተስፋ የገባልንን ምድር በጭፍን አንወርስም፤ መጀመሪያ መሰለል (ወርዱ፣ ስፋቱን፣ ይዘቱን ማየት) አለብን፡፡ «ከእናንተ ግንብ ሊሠራ የሚወድ ለመደምደሚያ የሚያበቃ ያለው እንደሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ ኪሣራውን የማይቆጥር ማን ነው? ያለዚያ መሠረቱን ቢመሠርት ሊደመድመውም ቢያቅተው ያዩት ሁሉ፡ -ይህ ሰው ሊሠራ ጀምሮ ሊደመድመው አቃተው ብለው ሊዘብቱበት ይጀምራሉ፤» ሉቃ. 14፡28-30፡፡

## ምዕ. 3፡ - የእስራኤላዊያን ዮርዳኖስን መሻገር

እስራኤላውያን ቀይ ባህርን የተሻገሩት ሙሴ ባህሩን ከከፈለላቸው በኋላ እንደሆነ በዘጸአት አይተናል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ግን ዮርዳኖስ እጅግ ሞልቶ ሳለ ታቦቱን የተሸከሙት የካህናት እግሮች በውኃው ዳር ሲጠልቁ ከላይ የሚወርደው ውኃ ቆመ (ኢያሱ 3፡15-16)፡፡

ይህ ምዕራፍ የሚያሳየን <u>የእምነትን እርምጃ</u> ነው፡፡ ካህናቱ፤ ይዞ በሚሄድ በጎርፍ ውሃ ላይ በእምነት ባይረግጡ ኖሮ ዮርዳኖስን መሻገርና፣ ማሻገር ምድሪቱንም መውረስና ማውረስ ባልቻሉም ነበረ፡፡ እኛም ብዙ መንፈሳዊ ርስቶችን የማንወርሰው መውሰድ ያለብንን የእምነት እርምጃ ስለማንወስድ ነው፡፡ «የእግራችሁ ጫማ የሚረግጠውን ቦታ ሁሉ ለእናንተ ሰጥቻለሁ» ሲል፤ የርስቱ ወርድና ስፋት የሚወሰነው እኛ በምንወስደው የእምነት እርምጃ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡

በዚህ ምዕራፍ የምናየው አንድ ትልቅ ነገር አለ፤ እርሱም ታቦቱን የተሸከሙት ካህናት ከፊት ቀድመው ዮርዳኖስን በመጀመሪያ መርገጥ ነበረባቸው (ቁ. 15-16)፡፡ በኋላም

በዮርዳኖስ መካከል ቆመው (ቁ. 17) ሕዝቡ በሙሉ (ወደ 3 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ) እስከሚያልፍ ድረስ መጠበቅ ነበረባቸው:: ሕዝቡ ሁሉ አልፎ ከጨረሰ በኋላ እነርሱ ከዮርዳኖስ ይወጣሉ ማለት ነው:: ወደ ዮርዳኖስ ለመግባት የመጀመሪያዎች ካህናቱ ነበሩ፤ ከዮርዳኖስ ለመውጣት ደግሞ የመጨረሻዎቹ እነዚያው ካህናት ነበሩ:: የሕዝቡ መንፈሳዊ መሪዎች ስለሆኑ ሕዝቡ በሚያጋጥመው ፈተናና ችግር ሁሉ ግንባር ቀዳሚዎችና ጠባቂዎች እነርሱ ናቸው::

## ምዕ. 4፡ - የመታሰቢያ ድንጋዮች፡ -

እግዚአብሔር ኢያሱን «በዮርዳኖስ መካከል የካህናት እግር ከቆመበት ስፍራ አሥራ ሁለት ድንጋዮች አንሡ ተሸክማችሁም በዚህ ሌሊት በምታድሩበት ሥፍራ አኑሯቸው ብለህ እዘዛቸው አለው» (ኢያ. 4፡3)::

በዚህ ምዕራፍ የምናየው <u>የእምነትን ምስክር</u> (መታሰቢያ) ነው:: በሚመጡ ዘመናት ለሚመጣው ትውልድ ሁሉ ምስክር እንዲሆን እግዚአብሔር ያዘዘው ትእዛዝ ነበረ:: እምነት ሁልጊዜ ትቶ የሚያልፈው ምስክርነት አለው::

## ምዕ. 5፡ - የአዲሱ ትውልድ በጌልጌላ መገረዝ

ከግብጽ ወጥቶ የነበረው ትውልድ ሁሉ ቢገረዝም በምድረ በዳ የተወለደው ትውልድ ስላልተገረዘ እግዚአብሔር ኢያሱን ወንዶቹን ሁሉ እንዲገርዛቸው ያዘዋል:: ከተገረዙ በኋላ፣ እግዚአብሔር ኢያሱን ፦ «ዛሬ የግብጽን ነውር ከእናንተ ላይ አንከባልያለሁ» ይለዋል::

በዚህ ምዕራፍ የምናየው «<u>የእምነትን መገረዝ</u> (ጥራት)» ነው::

በዮሐ. 15፡2 «... ፍሬ የሚያፈራውን ቅርንጫፍ ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል (ይገርዘዋል)» ይላል:: እምነት ካልተገረዘ ብዙ ፍሬ ሊያፈራ አይችልም::

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው ሌላ ነገር፤ እስራኤላዊያን ከተገረዙ በኋላ የመጀመሪያውን ፋሲካ በተስፋይቱ ምድር ሲያደርጉ እናያለን:: ፋሲካን ባደረጉ ማግስት የምድሪቱን ፍሬ

(እግዚአብሔር ከዘመናት በፊት የገባላቸውን ተስፋ) ከበሉ በኋላ በየዕለቱ ለ40 ዓመታት ከሰማይ ይዘንብላቸው የነበረው መና ይቀራል።

ከዚህ የምንማረው፤ እግዚአብሔር ለብዙ ዘመናት ሌሎች የለፉበትን መንፈሳዊ ምግብ እንደ መና እያዘነበልን ስንመገብ ኖረን ይሆናል። የእግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ ግን ከፊታችን ያለውን ዮርዳኖስን ተሻግረን (የእምነት እርምጃ ወስደን)፤ እምነታችን መገረዝ (መጥራት) ባለበት ሁሉ ተገርዘን <u>እግዚአብሔር ሊሰጠን ወደገባልን ተስፋ ገብተን የምድሪቱን ፍሬ ለራሳችን እንድንበላ እንጂ፤ ዕድሜ ልክ መናን ከሰማይ እየተጠባበቅን እንድንኖር አይደለም።</u> የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል፤ «ከጊዜው (በክርስትና ከቆያችሁበት ጊዜ) የተነሣ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነት ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋችኋልና፣ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም» ዕብ. 5፡12።

በአጭሩ የሚናገረው፤ ወደ ተስፋይቱ ምድር ተሻግራችሁ ከምድሪቱ ፍሬ መብላት ሲገባችሁ፣ አሁንም ከሰማይ መና ትጠባበቃላችሁ ማለት ነው። አሁንም ሌሎች እንዲግቱአችሁ ትጠብቃላችሁ።

## ለ. ተዋግቶ ጠላትን ከርስት ማስወገድ (ምዕ. 6-12)

በዚህ በሁለተኛው ክፍል <u>የምናየው የእምነት ተጋድሎና ድል</u> ነው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የእምነት ድል አድራጊነት፤ | ምዕ 6 | የኢያሪኮ መውደቅ |
| 2. | የእምነት መሰናክልና ውድቀት | ምዕ. 7 | የአካን ኃጢአት (ዕርም) |
| 3. | የእምነት መነሳት | ምዕ. 8 | የጋይ መደምሰስ |
| 4. | የእምነት መታለል | ምዕ. 9 | የገባዖን ሰዎች ሽንገላ |
| 5. | እምነት-ከአሸናፊዎች በላይ /More than conquerors/ | ምዕ. 10-12፡ | ኢያሱ ድል የመታቸው ነገሥታት |

## ምዕ. 6፡ - የኢያሪኮ መውደቅ

ይህ ምዕራፍ የሚያሳየው <u>የእምነትን ድል አድራጊነት ነው</u>፡፡ እግዚአብሔር ለኢያሱ፤ ለሰው አእምሮ የማይገባ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ረቂቅ የሆነ የጦር ስልት እንዲከተል ያዘዋል፡፡ ኢያሪኮ፣ እስራኤላውያንን ከመፍራት የተነሣ ተዘግታ (ተመሽጋ) ስለነበረ፣ እግዚአብሔር ኢያሱን፣ ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው፣ ሰባት ቀንደ መለከት ይዘው፣ ሰልፈኞችም ከእነርሱ ፊት ተሰልፈው፣ ሕዝቡ ደግሞ ታቦቱን የተሸከሙትን ካህናት ተከትሎ በ6 ቀናት ኢያሪኮን እንዲዞሩ፣ በ7ተኛው ቀን ግን 7 ጊዜ እንዲዞሩና በመለከትና በታላቅ ጩኸት እንዲጮኹ፣ ከዚያም የኢያሪኮ ግንብ ሁሉ እንደሚፈርስ ይነግረዋል፡፡ ኢያሱ፤ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ለአእምሮ የማይገባ ቢሆንም እንኳን እግዚአብሔር ያዘዘውን ሁሉ ያደርጋል፡፡ እግዚአብሔር እንዳለውም ከተማዪቱ በሙሉ በእስራኤል እጅ ትወድቃለች፡፡ ከዚህ ታሪክ የምንማረው፤ «በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፣ <u>በራስህም ማስተዋል አትደገፍ</u>፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን ዕወቅ፣ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል» (ምሳ. 3፡5-6) የሚለውን አምላካዊ ምክር ነው፡፡ በተጨማሪም፤ ከዚህ ምዕራፍ ጋለሞታይቱ ረዓብ ሰላዮቹን (ኢያሱ ምዕ. 2) ስለሸሸገችና በእስራኤል አምላክ ስላመነች እርስዋና ቤተሰቦችዋ እንዲሁም ቤተዘመዶችዋ እንደ ተረፉ እናያለን፡፡ «እርስዋም በእስራኤል መካከል እስከ ዛሬ ተቀምጣለች፡፡ (ኢያሱ 6፡25)፡፡ በሌላ ቦታ የእግዚአብሔር ቃል ሲመሰክርላት፣ «ጋለሞታይቱ ረዓብ ሰላዮችን በሰላም ስለተቀበለቻቸው ከማይታዘዙ ጋር በእምነት አልጠፋችም» (ዕብ. 11፡31) ይላል፡፡

## ምዕ. 7፡- የአካን ኃጢአት (እርም) እና የእስራኤል መሸነፍ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ፤ በአንድ ሰው መተላለፍ እስራኤላውያን ሁሉ ሲሸነፉና ሲያዝኑ እናነባለን፡፡ ከዚህ ምዕራፍ የምንማረው፤ በጠላቶቻችን ላይ ድልን የምንጎናጸፈው ከኃጢአትና ከእርም ነጻ ከሆንን ብቻ እንደሆነ ነው፡፡

ቁ 11-12 «እስራኤል በድሎአል፣ ያዘዝኳቸውንም ቃል ኪዳን ተላልፈዋል ... ስለዚህ የእስራኤል ልጆች በጠላቶቻቸው ፊት መቆም አይችሉም።»

በዚህ ምዕራፍ አካን በመበደሉ እርሱና ልጆቹ እንዲሁም ንብረቱ በሙሉ በድንጋይ ተወግሮ በእሳት ሲቃጠሉ እናያለን። ልጆቹ በእርሱ በደል ተቃጠሉ ማለት አንችልም። ልጆቹ ተባባሪዎች ባይሆኑ ኖሮ እግዚአብሔርን ቅን ፈራጅ አምላክ ስለሆነ፣ በቃሉም በሌላ ቦታ ልጅ በአባቱ ኃጢአት አይሞትም ስለሚል፤ አብረው እንዲሞቱ ባልተፈረደባቸው ነበረ (ሕዝ. 18፡19-20)።

ለዚህ ማስረጃ የሚሆነን በዘኍ. 16 ላይ ቆሬ በሙሴና በአሮን ላይ ተነሥቶ ባመጸ ጊዜ ቆሬና ከእርሱ ጋር የነበሩትን (ተባባሪዎቹን) ሁሉ መሬት ተሰንጥቃ እንደዋጠች እናነባለን። ነገር ግን ልጆቹ ከዚህ መቅሠፍት እንደተረፉ በዘኍ. 26፡11 ላይ እናነባለን።

ከዚህ ምዕራፍ የምንማረው ሌላ ነገር፤ በአንድ ወይም በጥቂት ሰዎች በደል የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ሊጠቃ እንደሚችል ነው። በተለይ በአንድ ልብ መሆን ባለበት ሕዝብ መካከል ዓመጽ ሲኖር ሕዝብ ሁሉ ይጎዳል፣ ይሸነፋል። ከዚህ ምዕራፍ የምናየው <u>የእምነትን መሰናክል</u> ነው።

<u>ምዕ. 8</u> እስራኤል ከጋይ ለሁለተኛ ጊዜ ተዋግተው እንዳሸነፉ እምነት ቢወድቅ እንኳን በእግዚአብሔር ምሕረትና ጸጋ እንደገና መነሣትና ያሸነፈውን ጠላት መደምሰስ እንዳለበት የሚያስተምር ምዕራፍ ነው።

ኃጢአት በእስራኤል መካከል ስለነበረ ጠላት አይሎ እስራኤል ቢሸነፍና ቢዋረድም፣ በእግዚአብሔር ፊት በመውደቅ ኃጢአትን ካስወገደ በኋላ ከእግዚአብሔር አዲስ መመሪያን በመቀበል ያሸነፈውን ጠላት ሲደመስስ እናያለን። «ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃል ሰባት ጊዜ ይነሳል።» ተብሎ እንደተጻፈ። በሕይወት ዘመናችን መውደቅ የማይቀር ነገር ነው፤ ነገር ግን በወደቅንበት ቦታ ቁጭ ማለት የለብንም። ኤርምያስ እንዲህ ይላል፤ «የወደቁ አይነሱምን? የሳተስ አይመለስምን?» (ኤር. 8፡4) ነቢዩ ሚክያስም፤ «ጠላቴ ሆይ <u>ብወድቅ እነሳለሁና</u> በጨለማም

ብቀመጥ እግዚአብሔር ብርሃን ይሆንልኛልና በእኔ ላይ ደስ አይበልሽ» ይላል (ሚክ. 7፡8)፡፡ ከዚህ ምዕራፍ የምናየው <u>የእምነትን እንደገና መነሳት</u> ነው፡፡

<u>ምዕ. 9፡</u>- የገባዖን ሰዎች እስራኤልን አታለው ቃል ኪዳን እንዳስገቧቸው እናነባለን፤

በዘዳ. 7፡2 እግዚአብሔር ለእስራኤል እንዲህ ብሎ አስጠንቅቋቸው ነበር፤ «አምላክህ እግዚአብሔርም በእጅህ አሳልፎ በሰጣቸው በመታህቸውም ጊዜ <u>ፈጽመህ አጥፋቸው ከእነርሱም ጋር ቃል ኪዳን አታድርግ አትማራቸውም</u>፡፡» ኢያሱ ግን ለሁለተኛ ጊዜ (የመጀመሪያው ጋይን ሊወጉ ሲሉ ነው፤ ምዕ. 7) የእግዚአብሔርን ምክር ሳይጠይቅ የገባዖን ሰዎች ያቀረቡትን ማስረጃ ብቻ በማየትና በማመን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ቃል ኪዳን ይገባላቸዋል፡፡ «ሰዎቹም ከሥንቃቸው ወሰዱ <u>እግዚአብሔርንም አልጠየቁም</u> ኢያሱም ከእነርሱ ጋር ሰላም አደረገ በሕይወት እንዲተዋቸውም ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ የማኅበሩም አለቆች ማሉላቸው፤ (ቁ. 14-15)፡፡

ጠላት ፊት ለፊት ተጋጥሞ ማሸነፍ ሲያቅተው፣ የሸንገላ ካባ ለብሶ አንደበቱን አለስልሶ በፍቅርና በትህትና አስመስሎ የእግዚአብሔርን ስምና ቃል እየተናገረ (የብርሃን መልአክ መስሎ) በመምጣት እምነታችንን ሊሸነግል ይሞክራል፣ ብዙ ጊዜም ይሳካለታል፡፡ እነዚህ የገባዖን ሰዎች የመጡት የእግዚአብሔርን ስም እየጠሩ የእርሱን ታላቅነት እያወጁ ነበረ፡፡

ቁ. 9-10 «ከአምላክህ ከእግዚአብሔር ስም የተነሣ እጅግ ከራቀ አገር ባሪያዎችህ መጥተናል ዝናውንም በግብጽም ያደረገውን ሁሉ በዮርዳኖስ ማዶም በነበሩት በሁለቱ አሞራውያን ነገሥታት በሐሴቦን ንጉሥ በሴዎን በአስታሮትም በነበረው በባሳን ንጉሥ በዐግ ያደረገውን ሁሉ ሰምተናል፡፡»

ኢያሱና ሽማግሌዎቹ እንደተታለሉ ባወቁ ጊዜ አንድ ጊዜ ምለውላቸዋልና ሊገድሏቸው ስለማይችሉ የእስራኤላዊያን ባሪያዎች አደረጓቸው፡፡ በዚህ ምዕራፍ የምናየው <u>የእምነትን መታለል</u> ነው፡፡ እግዚአብሔርን ካልጠየቅን (በራሳችን ማስተዋል ከተደገፍን) ሁልጊዜ እንታለላለን፡፡

ከምዕ. 10-12፡ - በከነዓን የነበሩ ነገሥታት በሙሉ ተባብረው በእሥራኤል ላይ እንደተነሱ፤ እስራኤልም ሁሉንም እንደደመሰሰ እናነባለን፡፡

በምዕ. 10 ላይ ኢያሱ ከአምስት ተባብረው ከመጡበት ነገሥታት ጋር ተዋግቶ ድል እንደነሣ እናነባለን፡፡ በዚህ ውጊያ ውስጥ የኢያሱንም የእግዚአብሔርንም ተዋጊነት እናያለን፡፡ ኢያሱ ቃል ኪዳን የገባላቸው የገባዖን ሰዎች በእነዚህ አምስት ነገሥታት ሲከበቡ ወደ ኢያሱም መልእክት በመላክ «ፈጥነህ ወደ እኛ ውጣ አድነንም» ይሉታል፡፡ ኢያሱም የሦስት ቀኑን መንገድ (ምዕ. 9፡17) በአንድ ሌሊት ገሥግሦ በድንገት መጣባቸው (ምዕ. 10፡9)፡፡ እግዚአብሔርም ከእስራኤል ጋር አብሮ ይዋጋ ስለነበር፤ «እግዚአብሔር ከሰማይ ታላላቅ የበረዶ ድንጋይ አወረደባቸውና ሞቱ፤ የእስራኤል ልጆች በሰይፍ ከገደሉአቸው ይልቅ በበረዶ ድንጋይ የሞቱት በለጡ» (ቁ. 11)፡፡

በኢዮብ. 38፡22-23 እንዲህ ይላል፤ «በውኑ ወደ በረዶው ቤተመዛግብት ገብተሃልን? የበረዶውንስ ቅንጣት ቤተ መዛግብት አይተሃልን? ይኸውም ለመከራ ጊዜ ለሰልፍና ለጦርነት ቀን የጠበኩት ነው፡፡»

ውጊያው በተጧጧፈ ጊዜ፤ «ኢያሱ እግዚአብሔርን ተናገረ፤ በእስራኤልም ፊት እንዲህ አለ፡- በገባዖን ላይ ፀሐይ ትቁም በኤሎንም ሸለቆ ጨረቃ፤ ሕዝቡም ጠላቶቻቸውን እስኪበቀሉ ድረስ ፀሐይ ቆመ ጨረቃም ዘገየ … እግዚአብሔር ለእስራኤል ይዋጋ ነበርና እግዚአብሔር የሰውን ቃል የሰማበት እንደዚያ ያለ ቀን ከዚያም በፊት ከዚያም በኋላ አልነበረም፡፡» (ኢያሱ. 10፡12-14) ከእግዚአብሔር ጋር አብረን በምንዘምትበት ጊዜ በፊታችን መቆም የሚችል ጠላት አይኖርም፡፡ «… ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና» 1ቆሮ. 3፡9፡፡

እግዚአብሔር ይህንን ታላቅ ድል ለሕዝቡ ከሰጠ በኋላ «በእስራኤል ልጆች ላይ ምላሱን ማንቀሳቀስ የደፈረ ማንም ሰው የለም» ይላል (ቁ. 21)፡፡ ሰይፋንና ክንዱን ቀርቶ «ምላሱን» ማንቀሳቀስ (በለሆሳስ እንኳን በእስራኤል ላይ ክፉ መናገር) የደፈረ የለም፡፡

የእግዚአብሔር ክብር በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ሲሆን ጠላት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ምላሱን ማንቀሳቀስ አይደፍርም፡፡

በሐዋርያትም እጅ ብዙ ምልክትና ድንቅ በሕዝብ መካከል ይደረግ ነበር፤ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው በሰሎሞን ደጅ መመላለሻ ነበሩ፡፡ ከሌሎችም አንድ ስንኳ ሊተባበራቸው የሚደፍር አልነበረም፤ ሕዝቡ ግን ያከብሩአቸው ነበር» ሐዋ. 5፡12-13፡፡ እንኳን ሊቃወሟቸው ሊተባበሯቸው እንኳን አልደፈሩም፡፡

በምዕ. 10፡24-25 ላይ ደግሞ ኢያሱ የሠልፈኞችን አለቆች በአምስቱ ነገሥታት አንገት ላይ እግራቸውን እንዲያኖሩ ሲነግራቸው እናያለን፡፡ «ኢያሱም፡- እግዚአብሔር በምትወጉአቸው በጠላቶቻችሁ ሁሉ ላይ እንዲሁ ያደርጋልና አትፍሩ፤ አትደንግጡ፤ ጽኑ፤ አይዞአችሁ አላቸው፡፡» በዚህ ጥቅስ ላይ፤ ኢያሱ በምዕ 1፡19 በእግዚአብሔር በተጽናናበትና በተበረታታበት ቃል ሌሎችን ሲያበረታታ እናያለን፡፡

በምዕ. 1፡9 «በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና፣ አይዞህ፣ አትፍራ፣ አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁምን? ይለዋል፡፡» እግዚአብሔር በመከራና በችግር ስናልፍ የሚያጽናናንና የሚያበረታታን፣ አንድ ቀን እኛም ሌሎችን እንድናጽናናና እንድናበረታታ ነው፡፡ 2ቆሮ. 1፡4 «እርሱ <u>በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል</u>፣ ስለዚህም <u>እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን</u>፡፡»

<u>በምዕ. 11</u> ላይ ከአሥር በላይ የሚሆኑ ነገሥታትና ቁጥር ስፍር የሌላቸው ሕዝቦች በእሥራኤል ላይ ሲሰለፉ እናያለን፡፡ እግዚአብሔር ኢያሱን፡- «ነገ በዚህ ጊዜ ሁሉን እንደሞቱ አድርጌ በእስራኤል እጅ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁና አትፍራቸው» ይለዋል፡፡ (ቁ. 6)

እግዚአብሔርም እንደተናገረው፤

«ኢያሱ ምድሪቱን ሁሉ ያዘ፤ ኢያሱም በእስራኤል እንደ ክፍላቸውና እንደ ነገዳቸው ርስት አድርጎ ምድሪቱን ሰጣቸው ምድሪቱም ከሰልፍ አረፈች» (ቁ. 23)።

<u>በምዕ. 12፤</u> ሙሴ በሕይወት እያለ ከዮርዳኖስ ወዲህ ማዶ ከተደመሰሱት ሁለት ነገሥታት ጀምሮ ኢያሱ የደመሰሳቸውን ነገሥታት በሙሉ ይዘረዝራል። በመጨረሻው ላይ እንዲህ ይላል፤

«... ነገሥታቱ ሁሉ ሠላሳ አንድ ናቸው» (ቁ. 24)። በዚህ ክፍል (ከምዕ. 10-12) የምናየው፤ <u>እምነት ከአሸናፊዎች ሁሉ በላይ እንደሆነ ነው</u>። 31 ነገሥታትን (አሸናፊ ነን ባዮችን) ደምስሶ ድልን ተጐናጸፈ።

«በዚሁ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።» ሮሜ 8፡37።

## ሐ. <u>ምድሪቱን መውረስ</u> ምዕ. - 13-24

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | ምድሪቱን መከፋፈል | ከምዕ. 13-19 | የእምነት ዋጋ |
| 2. | የመማጸኛ ከተማዎች | ምዕ. 20 | የእምነት ተገን |
| 3. | የሌዋውያን ድርሻ | ምዕ. 21 | የእምነት መጠበቅ |
| 4. | የሁለቱ ነገድ ተኩል መመለስና የምሥክር መሠዊያ መሥራት | ምዕ. 22 | የእምነት አንድነት |
| 5. | የኢያሱ ስንብት | ምዕ. 23-24 | የእምነት ጽናት |

ከምዕ. 13-19 የምናየው ኢያሱ ምድሪቱን ለ9 ተኩል ነገዶች ሲያከፋፍል ነው። በምዕ. 13፡1 እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ ይለዋል፤ «... አንተ ሸመገልህ በዕድሜህም አረጀህ ያልተወረሰች እጅግ ብዙ ምድር ገና ቀርታለች» በምዕ. 11፡23። ደግሞ «ኢያሱ ምድሪቱን ሁሉ ያዘ» የሚል ቃል እናነባለን። እነዚህ

ሁለት ጥቅሶች እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ሳይሆኑ እርስ በርስ የሚጣመሩ ናቸው። ምንም እንኳን ኢያሱ በምድሪቱ ላይ የነበሩትን ነገሥታት ሁሉ ደምስሶ ምድሪቱን ሁሉ ድል ቢያደርግም፤ ያ ድል የተደረገ ምድር ተከፋፍሎ በእያንዳንዱ ነገድ መወረስ ነበረበት። ምድሩ ሁሉ ድል ተደርጎ ነበረ፤ ምድሩ ሁሉ ግን ገና አልተወረሰም ነበረ።

በመንፈሳዊ ሕይወታችንም እንደዚሁ ነው፤ የይሁዳ አንበሳ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጨለማ ኃይላትን ሁሉ በመደምሰስ በመስቀል ላይ ድሉን አውጆልናል። «አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው» (ቆላ. 2፡15)። ይህም ሆኖ እያለ እያንዳንዱ ክርስቲያን ይህንን ጌታ የተቀዳጀለትን ድል ይዞ (ወርሶ) ይኖራል ማለት አይደለም። ይህንን ድል ወርሶ የሚኖር አለ፤ ይህንን ድል ሳይወርስ በጠላት እየተጠቃ የሚኖር ደግሞ አለ። የተሰጠንን ርስት መውረስና አለመውረስ የእኛ ኃላፊነት ነው። ጌታ የእርሱን ኃላፊነት ጨርሷል።

ምዕ. 13፡13 ላይ «የእስራኤል ልጆች ግን ጌሹራዊያንንና ማዕካታውያንን አላወጡም፣ እስከ ዛሬም ድረስ ጌሹርና ማዕካት በእስራኤል መካከል ይኖራሉ» ይላል። እነዚህ አሕዛቦች፤ ሙሴ ቀደም ብሎ የመታቸውና ድል ያደረጋቸው እንደነበሩ ከምዕ. 11 እና 12 እንረዳለን። እስራኤላውያን ግን ድርሻቸውን አልተወጡም። የተሸነፈን ጠላት ገፍቶ ማስወጣት አልቻሉም ወይም ሰነፉ።

ከቁ. 15-33፡ - ሙሴ ለሮቤልና ለጋድ ለምናሴም ነገድ እኩሌታ የሰጣቸውን ርስት ዳር ድንበር ይዘረዝራል።

## በምዕ. 14፡ - የካሌብን ርስት መውረስ እናያለን፤

ይህ የእግዚአብሔር ጀግና፣ የተሰጠውን የተስፋ ቃል ሳይረሳ ወይም ቸል ሳይል፤ ወደ ኢያሱ በመሄድ «ርስቴን ስጠኝ» በማለት ተዋግቶ ርስቱን ይጨብጣል። «ሙሴ በላከኝ ጊዜ እንደነበርኩ፣ ዛሬ ጉልበታም ነኝ፣ ጉልበቴም በዚያን ጊዜ እንደነበረ እንዲሁ ዛሬ ለመዋጋት ለመውጣትም ለመግባትም ጉልበቴ ያው ነው» ኢያሱ 14፡11። <u>እግዚአብሔር ጉልበቱ የሆነ</u>

ሰው ጉልበቱ ሁልጊዜ ያው ነው፤ ስለዚህ ነው ዳዊት እግዚአብሔርን «ጉልበቴ ሆይ እወድሃለሁ» የሚለው።

## ምዕ. 15፡ - የይሁዳ ነገድ የወረሱትን ርስት ዳር ድንበር ይዘረዝራል፤

ድንበሩን ከዘረዘረ በኋላ በቁ. 63 ላይ እንዲህ ይላል። «በኢየሩሳሌም የተቀመጡትን ኢያቡሳዊያንን ግን የይሁዳ ልጆች ሊያሳድዱአቸው አልተቻላቸውም፤ ኢያቡሳዊያንም እስከ ዛሬ በይሁዳ ልጆች መካከል በኢየሩሳሌም ውስጥ ተቀምጠዋል።»

ይህንን ጥቅስ ስናይ የይሁዳ ልጆች ቸልተኞች ሆነው ሳይሆን፣ «ሊያሳድዷቸው አልተቻላቸውም»። እግዚአብሔር ጠላቶችቻችን እስከ ተወሰነ ጊዜ በአጠገባችን እንዲቆዩ የሚፈቅድበት ጊዜ አለ። አንደኛው ምክንያት ውጊያን ሊያስተምረን ነው (መሳ. 3፡1-2) በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጳውሎስ እንደ እሾህ ይወጋው የነበረው የሰይጣን መልእክተኛ «ከእኔ እንዲለይ ሦስት ጊዜ ጌታን ለመንሁ። እርሱም ፀጋዬ ይበቃሃል፣ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ» ይላል (2ቆሮ. 12፡8-9)።

እነዚህ የይሁዳ ልጆች ሊያስወጧቸው ያቃታቸው ኢያቡሳውያን በተራራማ አገር የሚኖሩ (ዘኁ. 13፡29) እንደ ነበሩ እናነባለን። ሆኖም እግዚአብሔር ከፊታችሁ አባርራቸዋለሁ ካላቸው ሰባት አሕዛብ መካከል ናቸው። (ዘዳ. 7፡1-2)

«አምላክህ እግዚአብሔር ልትወርሳት ወደምትገባባት ምድር ባመጣህ ጊዜ ከፊትህም ብዙ አሕዛብን፣ ከአንተ የበለጡትን የበረቱትንም ሰባቱን አሕዛብን፣ ኬጢያዊውን፤ ጌርጌሳዊውንም፤ አሞራዊውንም፤ ከነዓናዊውንም፤ ፌርዛዊውንም፣ ኤዊያዊውንም ኢያቡሳዊውንም ባወጣ ጊዜ ፈጽመህ አጥፋቸው ከእነርሱም ጋር ቃል ኪዳን አታድርግ አትማራቸውም።» ከዚህ ክፍል እንደምንረዳው፣ እግዚአብሔር እነዚህን ሰባት አሕዛብ የሚያወጣበት የራሱ ጊዜ ነበረው። ሁሉንም በአንድ ጊዜ አላወጣቸውም። የይሁዳ ልጆችም ሊያወጧቸው ያልቻሉት ለዚህ ነበረ።

ከዘመናት በኋላ ኢያቡሳዊያንን ያስወጣ ዳዊት እንደሆነ እናያለን በ1ዜና. 11፡4-7 ተጽፍዋል።

በምዕ. 16፡ - የኤፍሬምን ልጆች (ከዮሴፍ ልጆች ታናሹ) ርስት ዳር ድንበር ይዘረዝራል፡፡

በዚህም ምዕራፍ «በጌዝርም የተቀመጡትን ከነዓናውያንን አላሳደዱአቸውም፣ እስከ ዛሬም ድረስ ከነዓናውያን በኤፍሬም መካከል ተቀምጠዋል፤ የጉልበት ግብርም ያስገብሩአቸው ነበር ይላል» (ቁ. 10)፡፡ ከእስራኤል ነገዶች መካከል ሙሉ በሙሉ ሳይወጡ ይቀመጡ ስለነበሩት አንዳንድ አሕዛቦች በመሳ. 3፡1-2 እንደዚህ ይላል፤ «ከከነዓናውያንም ጋር መዋጋት ያላወቁትን እስራኤልን በእነርሱ ይፈትናቸው ዘንድ፤ በፊትም ሰልፍን ያልለመዱ የእስራኤል ልጆች ትውልድ መዋጋትን ያውቁና ይማሩ ዘንድ እግዚአብሔር ያስቀራቸው አሕዛብ እነዚህ ናቸው፡፡...»

## በምዕ. 17፡- የምናሴ ነገድ የወረሰው ርስት ዳር ድንበር፤

በዚህም ምዕራፍ እንደገና ስለ ሰለጰዓድ አምስት ሴቶች ልጆች እናነባለን፡፡ በዘኍልቍ መጽሐፍ ጥናታችን ላይ ስለ እነዚህ አምስት የእምነት ሴቶች ጠቅሰን ነበረ (ዘኍ. 27፡1-11)፡፡ በዘኍ. 27 ላይ፣ ከሙሴ የተቀበሉትን የርስት ተስፋ በዚህ ምዕራፍ ከኢያሱ ተቀብለው ሲወርሱ እናነባለን (ኢያሱ. 17፡3-4)፡፡

በቁ. 14 ላይ ሁለቱ የዮሴፍ ልጆች፣ ኤፍሬምና ምናሴ ወደ ኢያሱ መጥተው፡ - «... እኔ ብዙ ሕዝብ ስለሆንኩ ... ለምን አንድ ዕጣ ብቻ ርስት አድርገህ ሰጠኸኝ፡፡» ሲሉት፤ ኢያሱ የሰጣቸው መልስ፤ «ብዙ ሕዝብስ ከሆንህ ተራራማውም የኤፍሬም አገር ጠቦህ እንደሆነ ወደ ዱር ወጥተህ ... ለአንተ ስፍራ መንጥር» የሚል ነበር (ቁ. 17-18)

ከኢያሱ መልስ የምንማረው፤ ተጨማሪ ርስት ወይም አዲስ ርስት ለማግኘት አዲስ ውጊያ መዋጋት (መመንጠር) ያስፈልጋል፡፡ ሳይዋጉ የሚወረስ ርስት የለም፡፡

## ምዕ. 18 እና 19፡ - የቀሩት ሰባት ነገዶች ርስት

ኢያሱ ለቀሩት ሰባት ነገዶች እንዲህ በማለት ይገስጻቸዋል፡፡

«... የአባቶቻችሁ አምላክ እግዚአብሔር የሰጣችሁን ምድር ትወርሱ ዘንድ እስከ መቼ ለመግባት ቸል ትላላችሁ?» ኢያ. 18፡3

ይህ ጥያቄ በጣም መሠረታዊ የሆነ ጥያቄ ነው፡፡ በዚያ ዘመን ለነበሩ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ብቻ ሳይሆን በዘመናት ሁሉ ላለነው የእግዚአብሔር ሰዎች የሚሆን ጥያቄ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ሕዝቡ እንዲወርስ የሚፈልገው ርስት (በረከት) አለው፡፡ እኛ ግን ቸል ካልን እግዚአብሔር ተስፋ የገባልን ርስት ቢሆንም እንኳን ሳንወርሰው እንዲሁ እንቀራለን፡፡ በዕብ. 6፡11 ይህንኑ ሐሳብ እናገኛለን፤ «በእምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ፣ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁን ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን፡፡»

ኢያ. ምዕ. 18 እና 19 በአጠቃላይ የሚናገረው እነዚህ ሰባት ነገዶች ሄደው ምድሪቱን እንደሰለሉና ኢያሱ ምድሪቱን ለሰባት ከፍሎ ዕጣ በመጣል እንዳከፋፈላቸው ነው፡፡ በመጨረሻ ላይ፤ አስራ አንዱ ነገዶች (ከሌዊ ነገድ በስተቀር፡- እግዚአብሔር ርስታቸው ነውና) ርስታቸውን ከወረሱ በኋላ ለኢያሱ አንዲት ከተማ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሲሰጡት እናያለን (ኢያ. 19፡49-50)፡፡

ከዚህ የምንማረው፤ የእግዚአብሔር ሰዎች መጀመሪያ ሕዝቡን (መንጋውን) ካሰማሩ በኋላ ነው ለራሳቸው ርስታቸውን የሚወርሱት፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ስለ ራሱ ሲናገር «የሰው ልጅ ሊያገለግል እንጂ ሊገለገል አልመጣም» ነው ያለው፡፡ መጀመሪያ የራሴን ድርሻ ላግኝ የሚል ምንደኛ እንጂ እውነተኛ እረኛ አይደለም፡፡

## በምዕ. 20፡- የመማጸኛ ከተሞችን ስለ መለየታቸው ይናገራል፤

ቁ. 2-3 «ሳይወድ ሳያውቅም ሰውን የገደለ ገዳይ እንዲሸሽባቸው በሙሴ እጅ የነገርኋችሁን መማፀኛ ከተሞችን ለዩ ከደም ተበቃዩ መማጸኛ ይሆኑላችኋል፡፡»

በአዲስ ኪዳን መማጸኛ የሆነልን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ከእግዚአብሔር ቃል እናያለን፡፡

2ኛዮሐ. 2፣1 «ልጆቼ ሆይ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ፡፡ ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ክርስቶስ ነው፡፡»

## ምዕ. 21 የሌዊ ነገድ በ12ቱ ነገዶች ሁሉ መካከል ርስትን መቀበል፡ -

የሌዊ ነገድ የተቀበለው ርስት ከሌሎች ሁሉ የሚለየው አንድ የተወሰነና በአራቱ አቅጣጫ ዳር ድንበር ያለው ርስት ሳይሆን፣ በ12ቱ ነገዶች ርስት መካከል ከእያንዳንዱ ነገድ የተወሰኑ ከተሞች ለሌዋውያን ተመድቦ ተሰጣቸው፡፡ ይህም ማለት ሌዋውያን በ12ቱም ነገዶች መካከል ተበትነው የሚኖሩ ነገድ ናቸው ማለት ነው፡፡ ይህ አሠራር ከሌዋውያን ኃላፊነት ጋር የሚሄድ እንደሆነ እናያለን፤ ምክንያቱም አንዱ የሌዋውያን ኃላፊነት የእግዚአብሔርን ህግ ለእስራኤል ማስተማር ነበረ፡፡ 12ቱም ነገዶች መካከል መበተን ነበረባቸው፡፡

ከቁ. 43-45 ስናነብ በአጠቃላይ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገላቸውን ይዘረዝራል፡፡ «እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ ለአባቶቻቸው የማለላቸውን ምድር ሁሉ ለእስራኤል ሰጠ፤ ወረሱአትም ተቀመጡባትም፡፡ … በዙሪያቸው ካሉት አሳረፋቸው ከጠላቶቻቸውም ሁሉ ይቋቋማቸው ዘንድ ማንም ሰው አልቻለም፤ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ሁሉ በእጃቸው አሳልፎ ሰጣቸው፡፡ እግዚአብሔር ለእስራኤል ቤት ከተናገረው መልካም ነገር ሁሉ ተፈጸመ እንጂ ምንም አልቀረም፡፡»

ከዚህ ክፍል የምንረዳው፤ እግዚአብሔር ለእስራኤል፤

1. ርስትን
2. ዕረፍትን
3. ድልን እንደ ሰጣቸው ነው

## ምዕ. 22፡ - የሮቤል፤ የጋድና የምናሴ ነገድ እኩሌታ የገቡትን ቃል በመጠበቅ ለወንድሞቻቸው ከተዋጉ በኋላ ኢያሱ ባርኮ ወደ ርስታቸው ይመልሳቸዋል (ከቁ. 1-6)፡፡

በሚቀጥለው ክፍል ደግሞ እነዚህ 2 ተኩል ነገዶች፣ ወደፊት፤ ከዮርዳኖስ ማዶ የወረሱት 9 ተኩሉ ነገዶች፣ ልጆቻችንን ከእኛ ጋር ምንም እድል ፈንታ የላችሁም፣ እግዚአብሔር በእኛና በእናንተ መካከል ዮርዳኖስን አድርጓል ብለው ከእግዚአብሔር ጉባኤ እንዳያርቋቸው ብለው በማሰብ አንድ <u>የምስክር መሠዊያ</u> ይሠራሉ፡፡ እነዚህ ነገዶች መሠዊያ እንደሠሩ 9 ተኩሉ ነገዶች በሰሙ ጊዜ እንዴት ከአንዱ መሠዊያ ሌላ መሠዊያ ትሠራላችሁ፣ እግዚአብሔርን ከመከተል ወደ ኋላ ብላችኋል በማለት 2 ተኩሉን ነገድ ለመውጋት ይሰበሰባሉ፡፡ በመጀመሪያ መልእክተኞችን (የነገድ ሽማግሌዎችንና የካህኑን የአልዓዛርን ልጅ ፊንሐስን) በመላክ ያደረጋችሁት ምንድነው? ብለው ሲጠይቋአቸው፤ ጉዳዩ ሌላ ሆኖ ተገኘ፡፡ እነርሱ እግዚአብሔርን በመፍራት ያደረጉት መልካም ነገር በመጥፎ ተተርጉሞባቸው ነበር፡፡

ይህ መጥፎ አተረጓጎም ሊመጣ የቻለው በመጀመሪያ «መሠዊያ ሠርተዋል የሚል ወሬ ደረሰላችው» (ቁ. 11) በሚለው ቃል መሠረት፤ ወሬውን ያመጣላቸው ሰው ቁንጽል ወሬ በማምጣቱ ነው፡፡ ከጅምሩ ሙሉ መረዳት ያለው ወሬ ቢመጣላቸው ኖሮ ወደ ፍልሚያ አይደርሱም ነበረ፡፡ የሠሩት <u>ምን ዓይነት መሠዊያ</u> እንደነበረ ማወቅ ነበረበት፡፡

በቤተ ክርስቲያንስ ስንት ጊዜ ነገሮችን አጣርተን ባለመረዳት፣ ጠላት በሚያመጣው ቁንጽል ወሬ ስንት ጦርነትና

ውጊያ ተነስቷል? በአገራችን «ያልሰማ ጆሮ ከጎረቤት ያጣላል» የሚለው አባባል ብዙ ጊዜ በእግዚአብሔር ሕዝብም መካከል እውነት ሆኖ እናገኘዋለን። መቼም ቢሆን በቁንጽል እውቀት ወደ ውሳኔ መድረስ የለብንም በመጀመሪያ ስለነገሩ ሙሉ እውቀትና መረዳት ይኑረን፣ ከብዙ አላስፈላጊ ጦርነትና ጉዳት ይጠብቀናል።

«... እግዚአብሔር አምላክ እንደሆነ ይህ በመካከላችን ምስክር ነው ሲሉ መሠዊያውን ምስክር ብለው ጠሩት» ቁ. 34።

## ምዕ. 23 እና 24፡ - የመጨረሻ ቃላት

ኢያሱ የእስራኤልን አለቆችና ሽማግሌዎች እንዲሁም እስራኤልን ሁሉ ሰብስቦ የሙሴን ህግ እንዲጠብቁና እግዚአብሔር አምላካቸውን ብቻ እንዲያመልኩና እንዲወዱ ያስጠነቅቃቸዋል።

ምዕ. 23 ቁ. 6 «በሙሴ ሕግ መጽሐፍ የተጻፈውን ሁሉ ለመጠበቅና ለማድረግ በጣም በርቱ ከእርሱም ወደ ቀኝም ወደ ግራም ፈቀቅ አትበሉ።» ይህ ቃል በኢያሱ 1፡7 ላይ እግዚአብሔር ኢያሱን ያዘዘው ቃል ነው።

ምዕ. 23 ቁ. 11 «አምላካችሁን እግዚአብሔርን ትወድዱት ዘንድ ለራሳችሁ እጅግ ተጠንቀቁ» ይላቸዋል።

«አምላካችሁ እግዚአብሔር ያዘዛችሁትን ቃል ኪዳን ስታፈርሱ ... በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ቁጣ ይነድድባችኋል ከሰጣችሁም ከመልካሚቱ ምድር ፈጥናችሁ ትጠፋላችሁ» ቁ. 16።

በምዕ. 24፡15 ላይ ኢያሱ ከሁሉ በላይ የታወቀበትን ጥቅስ እናነባለን፣ «የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ፣ <u>እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን</u>።»

ሕዝቡም ለኢያሱ «እግዚአብሔርን እናመልካለን» በማለት ደጋግመው ቃል ይገባሉ። ይህንንም ቃል እየገቡ እንኳን በመካከላቸው ሌሎች አማልክት ነበሩ።

«እርሱም፤ አሁን እንግዲህ <u>በመካከላችሁ ያሉትን እንግዶች አማልክት አርቁ</u>፣ ልባችሁንም ወደ እስራኤል አምላክ ወደ እግዚአብሔር አዘንብሉ አላቸው» (ቁ 23)።

«ኢያሱ ባለበት ዘመን ሁሉ፣ ከኢያሱም በኋላ በነበሩት ለእስራኤልም ያደረገውን የእግዚአብሔርን ሥራ ሁሉ ባወቁት ሽማግሌዎች ዘንድ ሁሉ፣ እስራኤል እግዚአብሔርን አመለኩ» (ቁ 31)።

ከዚህ ጥቅስ የምንማርው፤ እግዚአብሔርን ማወቅና እግዚአብሔርን ማምለክ አብረው የሚሄዱ ነገሮች እንደሆኑ ነው። አለበለዚያ «ለማይታወቅ አምላክ» ብሎ እንደማምለክ ይሆናል» (ሐዋ. 17፡23)።

## ምዕራፍ ሰባት፣ ጥያቄዎች

1. የመጽሐፈ ኢያሱ ዋና መልዕክት ምንድነው?
2. በመጽሐፈ ኢያሱና በኤፌሶን መልዕክት መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ግለጽ።
3. መጽሐፈ ኢያሱ በስንት ክፍሎች ይከፈላል? አከፋፈሉን ጥቀስ።
4. እግዚአብሔር የሰጠንን ርስት ከመውረሳችን በፊት መሰለል ለምን አስፈለገ?
5. በመሰለልና በመውረስ መካከል ምን እርምጃ አለ? ለምን?
6. ኢያሱ፤ በጋይ ሰዎች ሲሸነፍ በገባዖን ሰዎች ደግሞ ሲታለል እናያለን። በእነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ውስጥ የኢያሱ ተመሳሳይ ስህተት ምንድነው?

7. የገባዖንን ሰዎች አሠራር ስታይ ስለ ጠላታችን ዲያብሎስ ምን ትማራለህ?

8. በኢያሱ 18፤3 «እግዚአብሔር የሰጣችሁን ምድር /ርስት/ ትወርሱ ዘንድ እስከ መቼ ለመግባት ቸል ትላላችሁ?» ከሚለው ቃል ለግል ሕይወትህ ምን ትማራለህ?

9. በኢያሱ ምዕራፍ 22 የሮቤል፣ የጋድና የምናሴ ነገድ እኩሌታ ከዮርዳኖስ ወዲህ ማዶ ወደ ነበረው ርስታቸው ከተመለሱ በኋላ መሠዊያ በመሥራታቸው ከቀሩት እስራኤላዊያን ጋራ ጦርነት ሊነሳ የነበረበት ምክንያት ምንድነው? ከዚህ ሁኔታ ምን ትማራለህ?

*Global Good News Literature*

*P.O.Box 451336*

*Los Angeles, CA 90045*

(C) Copyright 2013 Global Good News Literature